# በቃ፤ በቃን እንበል

እስከመቼ በግዞት፣ በግፍ ወከባ እስራት፣
በመባረር ስቃይ ማየት፣ ተሰዶ ከሐገር መውጣት።
ሐገር ሐገር ሳትሆን፣ አስፈሪ ሁሉ የሚሸሻት፣
ሰቆቃ ረሃብ ችግር፣ በየረድፉ የሚታይባት።
ልስማሽ ዛሬ እማማ ኢትዮጵያ፣ ሐገሬ እሪ በይ ተጣሪ፣
እስከመቼ አቀርቅረሽ፣ በኛ አፍረሽ ልትኖሪ።
መለያሽ ሆኗል ረሃብሽ፣ ሲነጠቁ ልጆችሽ፣
ዓለም ጉድሽን እያየ፣ ምፀቱን ሲልክልሽ።
የእናቴ ገበና ሲወጣ፣ ልጅሽ ነኝና አፈርኩኝ፣
እስኪ መላውን ንገሪኝ፣ አሁንስ መግቢያ አጣሁኝ።
ትቼሽ ብወጣም አልቀረልኝ፣ ይከተለኛል በሄድኩበት፣
የእናትነት እንባ ለቅሶሽ፣ ጩኸትሽ ተሰማኝ ከርቀት።
አያስተኛኝም ሌሊትም፣ መቼ አግኝቼ ጥሩ እንቅልፍ፣
ስባንን ነው የማድረው፣ በቅዠት ዓለም ስልፈልፍ።
እስከመቼ ነው የሚቀጥል፣ የሰቆቃ ኑሮ በህዝብሽ፣
ቀና ብለሽ የምናይሽ፣ ካጎበጠሽ ምንተ እፍረትሽ።

መቼ ነው የሚያበቃው፣ በጠመንጃ አፈ ሙዝ መገዛት
የራስ ሐገር እንዳይደለ፣ ተሸማቆ መኖር በፍርሃት፣
የራስ መሬት እንዳልሆነ፣ መኖር ያለ ነፃነት።
ኢትዮጵያዊነቴን ልክድ? እሱማ ከቶ አይሆንም፣
ክብሬ ተዋርዶ ክብርሽን፣ ማዋረድ አይሆንልኝም።
በዘር መናቆር ጎሳ መለየት፣ በሃይማኖት መጋጨቱ፣
ሕዝብን እርስበርስ አባልቶ፣ የሥልጣን ወንበር ማቆየቱ፣
በቃን እንበል የሐገሬ ሰው፣ ይሰማን እንጂ ጉዳቱ።
በረሃብ የምንታወቅበት፣ ይታደስ ዛሬ ስማችን፣
በቃን ብለን እንነሳ፣ ይበልጣልና ክብራችን።

መሰደዳችን ይብቃ፣ ሞታችን ይሁን በሐገር፣
ምኑን ተሻለ የኛ ኖሮ፣ ከመሬት በታች ከመኖር።
ነፃነትን ተገፈን፣ ከመኖር እንደ እንስሳ፣
በቃ፣ በቃ እንበል ዛሬ፣ ለሐገር ክብር እንነሳ።
እጅ ለእጅ ተያይዘን፣ የፍቅር ጉዞ እንጀምር ፣
ይብቃን መለያየቱ፣ ጠላታችንም ይፈር።
ይበቃል ከእንግዲህ ወዲያ፣ የጨለማ ውስጥ ኑሮ፣
ማስማታችን ይቁም የሐዘን እንጉርጉሮ።
በቃ ብለን ተነስተን ድምፃችን ያስተጋባ፣
የአንድነት ባንዲራችንን፣ እንያት ተወለብልባ።
በነፃነት እንኑር፣ ሰብአዊነትም ይከበር፣
ዘርና ጎሳ ሳይለየን፣ በእኩልነት እንኑር፣
ለሁሉም እናት ትሁን፣ ጡት ነካሽ አይፈጠር፣
ኢትዮጵያችን ከፍ ትበል፣ ስሟም በመልካም ይቀየር።
ሁሉም ይቅር ተባብሎ፣ ያለፈው ጠባሳ ይጠገን፣
አዲስ ኢትዮጵያን እንፍጠር፣ በቃን ብለን ተነስተን።

ተባብረን የኢትዮጵያን ትንሣዔ እናፋጥነው።

ስለሺ ዘእንግልጣር